# ተዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል!



ጊዜው ተገልብጦ ታቹ ላይ ሆነና፣
ጀግና ነኝ ባይ ሁሉ ቆንጆ ሴት ተወና፣
በዝንጀሮ ቆንጆ እርስ በርስ ተብላላ፡፡

በሙዝ በበቆሎ ህሊና እየሸጡ፣
ሕዝብን ብዙ ዘመን በናዳ እንዳልፈጁ፣
ግመር ዝንጀሮች ጻድቆች ተባሉ፡፡

በዱባ እሚገዛ ሆዳምና ካድሬው፣
ተመቀመጫው ላይ ጠባሳው ቦግ ያለው፣
ዝንጀሮን አፍቅሮ ገደል መግባቱ ነው!

የዝንጀሮ ታሪክ አመልም ተሌለው፣
እንዴት በግመር ፍቅር ከንፎ ይሄዳል ሰው?

ተዝንጀሮ መንጋ ቆንጆ ሲፈልጉ፣
ብዙ ጂላጅሎች ተገደል ነጠሩ፡፡

ዝንጀሮ መረጣ ሲወጡ ሲወርዱ፣
የካቡትን ሁሉ እንደ ገደል ናዱ፡፡

ያልታደለ ገላ ያልተባረከ ነፍስ፣
በዝንጀሮ ቆንጆ ተለክፎ እንደ አንከሊስ፣
እንደ በላዔ ዘር እርስ በርስ መናከስ፡፡

ተሰው ልጅነቱ ታልወጣ በእርግማን፣
በዝንጀሮ ቆንጆ እንዴት ሰው ይጣላል?

በዝንጀሮ ቆንጆ ምርጫ ሲታገሉ፣
ባውሬ እየታደኑ ታንቀው ይበላሉ!

ያያቶችን ብሂል መከተሉን ትተው፣
“ተዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመርጧል?” ብለው፣
ወደቁና አለቁ ግመሮች አፍቅረው፡፡

ገደል ተመንጠልጠል ዝንጀሮ መረጣ፣
በድድ ለመናከስ እንደ ጅል ባላንጣ፣
ቆንጆ እምትዘፍንለት ለመሆን አርበኛ፣
እንደ አንበሳ አግስተህ ግባ ወደ ጫካ፡፡

ባራት እግር ቆመህ እንደ ከብት እንሰሳ፣
ተዝንጀሮ ቆንጆ መምረጡን ተውና፣
ቀጥ ብለህ የምትሄድ ሰው ሁን እንደገና!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
መጋቢት ሁለት ሺ አስራ አንድ ዓ.ም.